**አዋጅ ቁጥር ____/2014**

**የመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ**

ለሀገራችን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገት የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ የበለጠ ለማጎልበት ዘርፉ አስተማማኝ፤ የተቀናጀ፤ ዘመናዊና ደኅንነቱ የተረጋገጠ ሆኖ እንዲራመድ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የመንገድ ትራንስፖርት አደረጃጀትን የመንግሥትን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች ፖሊሲ በአግባቡ ለመተግበር አመቺ ሁኔታን በሚፈጥር መልኩ እንደገና ማዋቀር በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "**የመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር** ------ /2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1/ "**ሚኒስቴር**" ወይም "**ሚኒስትር**" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው።
2/ "**ድርጅት**" ማለት በንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ሥራ ላይ ለመሰማራት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሠረት የተቋቋመ እና በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገበ የህግ ሰውነት ያለው አካል ነው።

3/ **“ተቋም“** ማለት በትራንስፖርት ዘርፍ የተሰማራ እና በዚህ አዋጅ፣ በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ፤ በተሽከርካሪ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ አዋጅ እና በጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ዲመሬጅ ክፍያ አዋጅ መሠረት ቁጥጥር እና ክትትል የሚደረግበት መንግሥታዊ የሆነና መንግሥታዊ ያልሆነ ተቋም ነው።

4/ **“የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት”** ማለት በግለሰብ ወይም በድርጅት የሚከናወንና መንገደኞችን ወይም ዕቃዎችን በክፍያ የማጓጓዝ የንግድ ሥራ ሆኖ እንደሚከተለው የግል ወይም የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ተብሎ ተለይቷል፤

ሀ) **“የግል ንግድ የመንገድ ትራንስፖርት”** ማለት መንገደኞችን ወይም ዕቃዎችን የሚያመላልሰው ተሽከርካሪ ንብረትነቱ የድርጅት ሆኖ፤

i. የሚመላለሱት ዕቃዎች የዚያው ድርጅት ንብረት የሆኑ ወይም ለጥገና ወይም ለማደስ በአደራ የተሰጡ የሆኑ እንደሆነና ዕቃዎችን ማመላለስ ለድርጅቱ ዓይነተኛ የንግድ ሥራ አስፈላጊና ማሟያ የሆነ እንደሆነ፤

ii. የሚመላለሱት መንገደኞች የዚያው ድርጅት ሠራተኞች ሆነው የሚመላለሱትም ወደ ሥራ ቦታቸውና ከሥራ ቦታቸው የሆነ ወይም የድርጅቱን ሥራ ለማከናወን የሆነ እንደሆነ ነው።

ለ) **“የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት”** ማለት ከከተማ ታክሲ በስተቀር የግል ተብሎ ያልተመደበ ማንኛውም የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ነው።

5/ **“የዲስፕሊን መመሪያ”** ማለት በሚኒስቴሩ የወጣ የዲስፕሊን እርምጃ አወሳሰንና አፈፃፀም መመሪያ ነው።

6/ **“አውራ ጎዳና”** ማለት የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የሚያስተዳድረውና አውራ ጎዳና ብሎ የሚሰይመው መንገድ ነው።

7/ **“የስምሪት ፕሮግራም”** ማለት የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን የዓመት፤ የወር፤ የሳምንት ወይም የቀን አገልግሎትና እንቅስቃሴ የሚወስን የስምሪት መርሃ-ግብር ነው።

8/ **“የስምሪት መስመር“** ማለት በሚኒስቴሩ የሚወሰን የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ የስምሪት መነሻና መድረሻ ነው።

9/ **“መንገደኛ”** ማለት በተሽከርካሪ ተሳፍሮ የሚሄድ ማንኛውም ሰው ሲሆን ነጂውን፤ ገንዘብ ተቀባዩንና በተሽከርካሪው ላይ የተመደበ ማንኛውንም ሌላ ሠራተኛን አይጨምርም፤

10/ **"ቁጥጥር"** ማለት በዚህ አዋጅ፤ በአዋጁ መሠረት የሚወጡ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ደረጃዎች እና ውሳኔዎች በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውን የማረጋገጥ ተግባር ነው፤

11/ **"መንገድ"** ማለት በተለምዶ ተሽከርካሪዎች የሚጠቀሙበት ማንኛውም ጎዳና፤ የከተማ መንገድ፤ አውራ ጎዳና ወይም መተላለፊያ ሲሆን ድልድይንም ይጨምራል።

12/ **"ተሽከርካሪ"** ማለት ልዩ ወታደራዊ ተሽከርካሪዎችን ሳይጨምር በመንገድ ላይ በመንኮራኩር የሚሄድ ማንኛውም ዓይነት ተሽከርካሪ ሆኖ ሰረገላን፣ ሳይክልን ፣ባለሞተር ተሽከርካሪን፣ ግማሽ ተሳቢን እና ተሳቢን ያጠቃልላል።

13/ **"ሠረገላ"** ማለት ከብስክሌት፣ ከባለሞተር ተሽከርካሪ፣ ከግማሽ ተሳቢ እና ከተሳቢ በስተቀር ማንኛውም ተሽከርካሪ ነው።

14/ **"ሳይክል"** ማለት በሚነዳው ሰው ኃይል እና/ወይም በኤሌክትሪክ ኃይል እየተንቀሳቀሰ የሚሄድ ተሽከርካሪ ነው።

15/ **"ባለሞተር ተሽከርካሪ"** ማለት በመካኒካል ወይም በኤሌክትሪክ ኃይል እየተንቀሳቀሰ የሚሄድ ተሽከርካሪ ሆኖ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ፣ ባለሞተር ብስክሌት፣ የግል አውቶሞቢል፣ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ፣ ጎታች መኪና እና ልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያን ያጠቃልላል።

16/ **"የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ"** ማለት ማንኛውንም ዓይነት ዕቃ እንዲያመላልስ ተብሎ የተሠራና ለዚሁ አገልግሎት እንዲውል የተደረገ ባለሞተር ተሽከርካሪ ሲሆን ጎታች መኪናን ይጨምራል።

17/ **"ባለሞተር ብስክሌት"** ማለት የጎን ተሽከርካሪውን ሳይጨምር ክብደቱ ከ400 ኪሎ ግራም የማይበልጥ ከአራት መንኮራኩር በታች ያለው ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው።

18/ **"የግል ተሽከርካሪ"** ማለት ከጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ፣ ከባለሞተር ብስክሌት፣ ከሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ፣ ከጎታች መኪና እና ከልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያ የተለየ ለግል መጠቀሚያ የሚውል ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤

19/ **"የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ"** ማለት መንገደኞችን ለማመላለስ የሚያገለግል ባለሞተር ተሽከርካሪ ሲሆን የንግድ አውቶሞቢልና አውቶቡስን ያጠቃልላል።

20/ **"የንግድ አውቶሞቢል"** ማለት ከአስራ ሁለት የማይበልጡ መንገደኞችን የሚያሳፍር የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ነው፤

21/ **"አውቶቡስ"** ማለት የታክሲ አገልግሎት ከሚሰጡት በስተቀር ከአስራ ሁለት መንገደኞች በላይ ለማሳፈር የሚችል የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ነው፤

22/ **"ጎታች መኪና"** ማለት በተለይ ሌሎች ተሽከርካሪዎችን ለመጎተት የሚያገለግል ሆኖ የሌላ ጭነትን ሳይሆን የሚጎትተውን ተሽከርካሪና በተጎታቹ ላይ ያለውን ጭነት ክብደት ብቻ በከፊል ለመሸከም የተሠራ ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤

23/ **"ልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያ"** ማለት ሰውን ወይም ዕቃን በመንገድ ላይ እንዲያመላልስ ሆኖ የተሠራ ተሽከርካሪ ሳይሆን ለእርሻ፣ ለአትክልት፣ ለከብት እርባታ፣ ለመንገድ፣ ለሕንጻ፣ ለቁፋሮ ወይም ለማንኛውም ተመሳሳይ ሌላ ሥራ የተሠራ ወይም ለዚሁ ጉዳይ እንዲውል የተደረገ ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤

24/ **"ግማሽ ተሳቢ"** ማለት ለመንገደኞች ወይም ለጭነት ማመላለሻ የሚያገለግልና በሌላ ባለሞተር ተሽከርካሪ የሚሳብ ሆኖ የተሽከርካሪውም የጭነቱም ክብደት በከፊል በሌላ ተሽከርካሪ ላይ እንዲያርፍ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ እንዲሳብ ተደርጎ የተሠራ ተሽከርካሪ ነው፤

25/ **"ሙሉ ተሳቢ"** ማለት ለራሱ የተለየ የሞተር ኃይል የሌለው ሆኖ ጎታች በሆነ በሌላ ባለሞተር ተሽከርካሪ ላይ ሊቀጠልና ሊጎተት የሚችልና ክብደቱ ጎታች በሆነው ባለሞተር ተሽከርካሪ ላይ እንደማያርፍ ሆኖ የተሠራ ተሽከርካሪ ነው፤ ሆኖም ከባለሞተር ብስክሌት ጋር ተያይዞ የሚሳበውን የጎን ተሽከርካሪ አይጨምርም፤

26/ **"ሞተር አልባ የትራንስፖርት መገልገያ"** ማለት በመካኒካል ወይም በኤሌክትሪክ ኃይል እየተንቀሳቀሱ ከሚሄዱ ተሽከርካሪዎች በስተቀር ማናቸውም ሞተር አልባ የሆኑ የትራንስፖርት መገልገያ መሣሪያዎች ማለት ነው።

27/‹‹**የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት መናኸሪያ**›› ማለት የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች መንገደኞችን ወይም ዕቃዎችን እንዲጭኑበት/እንዲያራግፉበት ታስቦ የለማ መሰረተ-ልማት ነው፡፡

28/ "**የአውቶቡስ ዴፖ**" ማለት የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ አውቶቡሶች ለጥገና፣ ለመታጠቢያ፣ ነዳጅ ለመቅዳት እና ለማደር በጋራ እንዲጠቀሙበት ታስቦ የለማ መሰረተ-ልማት ነው፡፡

29/"**የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት መናኸሪያ**" ማለት የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች ጭነቶችን እንዲጭኑበት፣ እንዲያራግፉበት፣ እንዲያሽጉበት እና እንዲበትኑበት ታስቦ የለማ መሰረተ-ልማት ማለት ነው፡፡

30/“**መጋዘን**” ማለት የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት መነሻ ወይም መድረሻ ሆኖ እንዲያገለግል ታስቦ የለማ የጋራ መስረተ-ልማት ነው፡፡

31/ **"የሀገር ውስጥ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት"** ማለት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ክልሎችን በሚያገናኝ መንገድ ላይ የሚከናወን የንግድ መንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ነው፡፡

32/ **"ክልል"** ማለት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 47 መሠረት የተቋቋመ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

33/ **"ዓለም-አቀፍ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት"** ማለት የኢትዮጵያን ድንበር አቋርጦ የሚካሄድ ድንበር አቋራጭ የንግድ መንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ነው፤

34/ **"ቢሮ"** ማለት የትራንስፖርት ሕጎችን የሚያስፈፅም የክልል አስፈፃሚ አካል ነው፤

35/ **"ልዩ ሥልጠና"** ማለት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ላለው አሽከርካሪ ለልዩ የአሽከርካሪ ባለሙያነት በሚኒስቴሩ ወይም በክልል ተለይቶ የሚሰጥ ሥልጠና ነው፤

36/ **"መደበኛ ሥልጠና"** ማለት የአሽከርካሪ ብቃት ለሌለው ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ ወይም አስቀድሞ የያዘውን የአሽከርካሪነት ብቃት ምድብ ለመቀየር ወይም ለማሳደግ የሚሰጥ ሥልጣና ነው፤

37/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት ችሎታ የተሰጠው ነው፡፡

38/ በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴት ጾታንም ያጠቃልላል፡፡

## 3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ ሁለትና ከሁለት በላይ ክልሎችን በሚያገናኙ መንገዶች ላይ በሚሰጡ የትራንስፖርት አገልግሎትና መሰረተ-ልማቶች፤ በመንገዶች በሚገለገሉና በሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎችና አሽከርካሪዎች እንዲሁም የመንገድ ተጠቃሚዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. የአዋጁ ዓላማዎች

የአዋጁ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

1/ አስተማማኝ፤ የተቀናጀ፤ ዘመናዊና ሁሉን አቀፍ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ተደራሽነትን ማረጋገጥ፤
2/ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ደኅንነትን ማረጋገጥ፤
3/ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ከአካባቢ ብክለት የጸዳና ለአካባቢ ተስማሚ መሆኑን ማረጋገጥ፤
4/ ቀጠናዊ የትራንስፖርት ትስስርን በማጠናከር ቀልጣፋ ዓለም ዓቀፍ የሎጂስቲክስ አፈጻጸም ውጤታማነትን ማጎልበት፤
5/ ሀገር ዓቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት የተሳለጠና ተመጋጋቢ እንዲሆን ማድረግ፤

## ክፍል ሁለት

## ስለሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር

## 5. የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር

ሚኒስቴሩ በፌደራል አስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 የተሠጡት ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው በተለይ የመንገድ ትራንስፖርትን በተመለከተ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1/ የመንገድ ትራንስፖርትን የሚመለከቱ የፖሊሲ ሐሳቦችንና ህጎችን ያመነጫል፣ ሲጸድቁም ተግባራዊ ያደርጋል፤ አፈጻጸማቸውንም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
2/ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ደኅንነቱ የተረጋገጠ፣ ቀልጣፋ፣ አስተማማኝ፤ ፍትሃዊ እና ተደራሽ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችሉ ተግባራትን ያከናውናል፤ እንዲከናወኑ ያደርጋል፤ ያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል፤
3/ በአካል ጉዳት ምክንያት ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የመንገድ ተጠቃሚዎች ምቹ የሆነ የመንገድ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤ አተገባበሩ ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤
4/ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን የመንገድ ትራንስፖርትን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ፤ አህጉራዊና ቀጣናዊ ስምምነቶች ተግባራዊነት በሀገር አቀፍ ደረጃ ይከታተላል፤

5/ ሁለት እና ከሁለት በላይ የሆኑ ክልሎችን የሚያገናኙ አውራ ጎዳናዎች ላይ የሚከናወኑ የትራንስፖርት አገልግሎቶችን ያስተዳድራል፤ ይቆጣጠራል፤ የትራንስፖርት አገልግሎቶችን ተደራሽነት ያረጋግጣል፤

6/ በኢትዮጵያ ውስጥ የተቀናጀ የሕዝብ ማመላለሻና የዕቃ ማጓጓዣ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ሥርዓት እንዲስፋፋ፤ መንገደኞች፣ ዕቃዎችና ፖስታዎች በንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ስለሚጓጓዙበት ሁኔታ የአሰራር መመሪያ ያወጣል አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

7/ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ሥራ ላይ በተሰማሩ ግለሰቦች እና ድርጅቶች የገበያ እጦት ሲያጋጥም ወይም ለተገልጋዩ ህብረተሰብ የመንገድ የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦት እጥረት ሲከሰት ተገቢውን ክትትል በማድረግ የመፍትሄ እርምጃዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በገበያ ስርዓት መሠረት አገልግሎት እንዲሰጡ ያደርጋል፤

8/ በህዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ የሚሰማሩ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የሚያቀርቡለትን የስምሪት ፕሮግራም መርምሮ ያጸድቃል፤ የስምሪት ፕሮግራሙ ፍትሃዊነትና አተገባበር ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤ የስምሪት ፕሮግራም ካልቀረበለትም በራሱ አዘጋጅቶ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤ ለዚሁ የወጣውን የዲሲፕሊን መመሪያ ይተገብራል፤

9/ የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም ጊዜያዊ የኢኮኖሚ ወይም የማህበራዊ ችግሮች ሲከሰቱ ወይም ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን በአስፈላጊው ቦታና መስመር በመደልደል እንዲሰማሩ ያደርጋል፤ ስምሪቱን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

10/ በሀገር ውስጥና ዓለም-ዓቀፍ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ወይም ድርጅቶች የሚያቋቁማቸውን የንግድ ተቋሞች የትራንስፖርት አሰራር የሚመለከት መመሪያ ያወጣል፤ ለነዚህ ሰዎችና ድርጅቶች የሙያ ብቃት ደረጃ እና የኦፐሬተርነት ብቃት መስፈርት ይወስናል፤ የሙያ ብቃትና የኦፐሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፤ ያድሳል፤ ይሰርዛል፤ ለድንበር አቋራጭ ተሽከርካሪዎች ፈቃድ ይሰጣል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

11/ በሀገር ውስጥ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ወይም ድርጅቶች የሚያስከፍሉትን ታሪፍ በተመለከተ ለሚሰጡት አገልግሎት ማግኘት ስለሚገባቸው ጥቅም እና የተጠቃሚዎችን የመክፈል አቅም በሚመለከት በየጊዜው ጥናት ያካሂዳል፤ የአገልግሎት ሰጪውንና የአገልግሎት ፈላጊውን ጥቅም እና አቅም ግምት ውስጥ በማስገባት የታሪፍ መጠኑን ሊወስን ይችላል፤

12/ በዓለም ዓቀፍ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚስፋፋበትን ሁኔታ እያጠና ተግባራዊ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

13/ በዓለም ዓቀፍ ትራፊክ የሚሰማሩ ተሽከርካሪዎችንና አሽከርካሪዎችን አመዘጋገብ ሥርዓት ይወስናል፤ የአሽከርካሪዎችንና የተሽከርካሪዎቹን የምዝገባ ሰርተፊኬት ወይም ልዩ ፈቃድ ይሰጣል፤ ሌሎች የተሽከርካሪዎቹን መለያዎች ይወስናል፤ ፈቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤ ዓለም አቀፍ የመንገድ ትራፊክን ያስተዳድራል፤

14/ ከመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ በማንኛውም አካል መካከል አለመግባባትና ክርክር ሲፈጠር እና ባለጉዳዮቹ ሲጠይቁ በግልግል አይቶ ይወስናል፤ እንዲሁም በሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ ክልሎች መካከል የትራንስፖርት አገልግሎትን አስመልክቶ አለመግባባት ቢፈጠር አለመግባባቱ ላይ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሰጣል አፈጻጸሙን ያረጋግጣል፤

15/ በኢትዮጵያ ውስጥ የሞተር አልባ ትራንስፖርት ከሀገራችን ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ እና አየር ንብረት ጋር በሚጣጣምና ለተጠቃሚው በሚያመች መልኩ እንዲስፋፋ ያደርጋል፤ የማበረታቻ የአሰራር ሥርዓቶችን ይዘረጋል፤ አተገባበራቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

16/ መንገዶችን የሚጠቀሙ ባለሞተር ተሽከርካሪዎች በሚሰጡት አገልግሎት ዓይነት ሊኖራቸው የሚገባውን ክብደትና መጠን እንዲሁም የተሳፋሪን ብዛትና የጭነት ክብደት ይወስናል፤

17/ ከውጭ ሀገር የሚመጡትን፤ በሀገር ውስጥ የሚሠሩትንና የሚገጣጠሙትን ወይም በከፊል የሚሠሩትን ወይም በሥራ ላይ የተሰማሩ ማናቸውም ዓይነት ባለሞተር ተሽከርካሪዎች የዕድሜ ገደብ በማስወሰን ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ ለዚሁም መመዘኛ የሚያገለግል ዝርዝር መስፈርት ያወጣል፤ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

18/ የመንገድ ደህንነት ደረጃዎችን ያዘጋጃል፤ በነዚህ ደረጃዎች መሠረት የተሽከርካሪዎችን አመዘጋገብና የቴክኒክ ምርመራ የሚመለከት መመሪያ ያወጣል ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

19/ ማናቸውንም የተሽከርካሪ ጋራዥ የቴክኒክ ብቃት ለማረጋገጥ፣ የሥራ ፈቃድና ዕድሳት አሰጣጥ እና ደረጃውን ለመወሰን የሚያስችል መመሪያ ያወጣል፤ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፤ ያድሳል፤ ይሰርዛል፤

20/ ተሽከርካሪዎች እንደገና ስለሚሠሩበት፣ ስለሚፈቱበት ወይም ይዘታቸውንና አገልግሎታቸውን ስለሚቀይሩበት ሁኔታ; አገልግሎት የማይሰጡና ከጥቅም ውጭ የሆኑ ተሽከርካሪዎች ወይም በዕድሜ ገደብ ምክንያት አገልግሎት እንዳይሰጡ የሚደረጉ ተሽከርካሪዎች ስለሚወገዱበት ሁኔታ መመሪያና የአሰራር ሥርዐት በማውጣት ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

21/ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት እንቅስቃሴን የሚመለከቱ መረጃዎችን በቴክኖሎጂ በተደገፈ አሰራር ይቆጣጠራል፣ መረጃ ያጠናቅራል ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል።

22/ የባለሞተር ተሽከርካሪዎች ማቆሚያን፣ የህዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያዎችን፥ የአውቶቡሶች ዴፖን፥ የጭነት ተርሚናሎችን ደረጃዎች ይወስናል፥ አተገባበራቸውን ይከታተላል፥ እንደአስፈላጊነቱም እነዚህን የትራንስፖርት መሠረተ-ልማቶች ያስፋፋል፤ ያስተዳድራል።

23/ የባለሞተር ተሽከርካሪዎችን የቴክኒክ ምርመራ የሚያከናውኑ፤ የልዩ ማሽነሪ አሽከርካሪነትን ጨምሮ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ሥልጠና የሚሰጡ ተቋማትን ደረጃ ይወስናል፤ ለእነኚህና ለአሽከርካሪ አሠልጣኞች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሠጣል፤ ያድሳል፤ ይሰርዛል፤ የሚመለከታቸው አካላት የሚያከናውኑትን የብቃት ማረጋገጫና የሥራ ፈቃድ አሰጣጥ ይመረምራል፤ ይቆጣጠራል፤ አሰራራቸውን ይከታተላል፤

24/ የተለያዩ ዓይነት ተሽከርካሪዎችን ለማሽከርከር የሚያስችሉ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫዎችን ደረጃ፤ ዲዛይን፤ ቀለም ዝርዝር ይዘታቸውን ይወስናል፤ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ይወስናል፤ አፈጻጸማቸውን ይቆጣጠራል፤

25/ በፌደራል ደረጃ ወይም በክልል ቢሮዎች በሚመዘገቡ ማናቸውም ዓይነት ተሽከርካሪዎች ላይ ለሚለጠፍ ሠሌዳ ዝርዝር መስፈርት ያወጣል፤ እንዲመረት ያደርጋል፣ ስርጭቱንና አጠቃቀሙን ይከታተላል፣ አገልግሎታቸውን የጨረሱ ሠሌዳዎች የሚወገዱበትን እና ባለቤታቸው ጠፍቶ ብዙ ጊዜ የቆሙ ተሽከርካሪዎች የሚሰበሰቡበትንና የሚወገዱበትን ሁኔታ ይወስናል፤ አፈጻጸማቸው ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤ ሠሌዳ ለሌላቸው አዲስ ተሽከርካሪዎች ለአንድ ጊዜ ጉዞ ብቻ የሚያገለግል መሸኛ ይሰጣል፤

26/ ተግባርና ኃላፊነቱን በአግባቡ ለመፈፀም እንዲቻለው ተቆጣጣሪዎችን በቋሚነትም ሆነ በጊዜያዊነት በማንኛውም የኢትዮጵያ ክልል ውስጥ ሊመድብ ይችላል፤

27/ የመንገድ ትራንስፖርት ዘርፉንና የተጠቃሚውን ህብረተሰብ ደኅንነት በሚጎዳ ወይም አደጋ ላይ በሚጥል በማንኛውም አካል ላይ ተገቢው ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

28/ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎቶች በአካባቢና አየር ንብረት የሚኖራቸውን ተፅዕኖ ለመቀነስ የሚያስችሉ ስልቶችን በመለየትና ከሌሎች አካላት ጋር በመተባበር በሥራ ላይ ያውላል፤ አተገባበራቸውን ይቆጣጠራል፤

29/ በትራንስፖርት ዘርፍ የተሰማሩ ሰዎች፤ ድርጅቶች እንዲሁም የሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና ተጠቃሚ ህብረተሰብ የሚወከሉበት አማካሪ ጉባዔ ሊያቋቁም ይችላል፤

30/ የመንገድ ትራንስፖርት ዘርፉን ለማዘመን የመንገድ ትራንስፖርትን የሚመለከቱ ሀገር አቀፍ መረጃዎችን ለመሰብሰብ፣ ለማደራጀት እና ለማሰራጨት የሚያስችል

የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ማዕከል ያደራጃል፤ የመረጃ ሥርጭት ሥርዓትን በመዘርጋት የሚመለከታቸው አካላት ጥቅም ላይ እንዲያውሉት ያደርጋል፤

31/ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎትን ለማቀላጠፍና ደህንነቱን ለመጠበቅ በተሽከርካሪዎች ላይ የሚገጠሙ ወይም በአሽከርካሪዎች የሚተገበሩ ቴክኖሎጂዎችና የመገናኛ ቁሳቁሶችን ደረጃ ከሚመለከተው አካላት ጋር በመተባበር ይወስናል፣ ይህን አገልግት ለሚሰጡ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

32/ ዓለም ዓቀፍ የማኔጅመንት መስፈርቶችን ተጠቅሞ የትራንስፖርት ቢሮዎችን እና የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎችን የአፈጻጸም ደረጃ በየዓመቱ ይፋ ያደርጋል፣

33/ በንግድ የመንገድ ማመላለሻ ስራ ላይ የሚሰማሩ ወይም ንብረትነታቸው የዲፕሎማቲክ፤ የዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች፤ ከአንድ ክልል በላይ የሚንቀሳቀሱ የተራድኦ ድርጅቶች ወይም የፌዴራል መንግስት የሆኑ ባለሞተር ተሽከርካሪዎችን በራሱ ወይም ውክልና በሰጠው አካል መመዝገባቸውንና የቴክኒክ ምርመራ ማድረጋቸውን ይከታተላል፤ ቁጥጥር ያደርጋል፤

34/ ዓለም ዓቀፍና የሀገር ውስጥ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት መሥመሮች ላይ ፍትሃዊ የስምሪት አገልግሎት እና አቅርቦት መኖሩን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

35/ ኢትዮጵያ አባል በሆነችበት የሦስትዮሽ የትራንስፖርትና የትራንዚት ፋሲሊቴሽን ፕሮግራም ላይ ኢትዮጵያን ወክሎ ይሳተፋል፤ በፕሮግራሙ ውስጥ የተካተቱና ሚኒስቴሩን የሚመለከቱ ተግባራትን ያከናውናል፤ በሀገር ዓቀፍ ደረጃም አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

36/ የገጠርና የከተማ መንገዶችን በሚያስተሳስሩ መንገዶች ላይ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲስፋፋ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

37/ ለልዩ አገልግሎት ተብለው የተሰሩ ወይም የተሻሻሉ ተሽከርካሪዎችን የሚመለከት ዝርዝር የቴክኒክ መስፈርት ያዘጋጃል፤ ይመዘግባል፤ ተሽከርካሪዎቹ ለተሰሩበት ወይም ለተሻሻሉበት ልዩ አገልግሎት ብቻ ስለማዋላቸው ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

38/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማበረታቻ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን በዘርፉ የተሰማሩ ድርጅቶችና ተቋማትን በመለየት ለሚመለከተው የመንግሥት አካል በማቅረብ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

39/ ታዳሽ ኃይልን የሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎች በኢትዮጵያ ውስጥ የሚስፋፉበትን መንገድ እያጠና ተግባራዊ ያደርጋል፤ ለታዳሽ ኃይም ተጠቃሚ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚሰጡ የመሰረተ-ልማት አገልግሎቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

40/ በማንኛውም ዓይነት ኃይል የሚንቀሳቀሱ አዲስ ተሽከርካሪዎችን ለሚያመርቱ፤ ሙሉ ለሙሉ ለሚገጣጥሙና በከፊል ለሚገጣጥሙ አምራቾችና ገጣጣሚዎች፤ አዲስ ተሽከርካሪ ወደሀገር ውስጥ ለሚያስመጡ አስመጪዎች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፤ ያድሳል፤ ይሰርዛል፤

41/ በሀገራችን ውስጥ የባለሞተርና ሞተር አልባ ተሽከርካሪዎች ማምረቻና መገጣጠሚያ ኢንዱስትሪ እንዲስፋፋ እገዛ ያደርጋል፤ ለዚህ ኢንዱስትሪ መስፋፋት ምቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ የሚመለከታቸውን አካላት በማቀናጀት ያስተባብራል፤ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

## ክፍል ሦስት

## የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት

### 6. ንግድ ፈቃድ አስፈላጊ ስለመሆኑ

1/ በንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ሥራ ላይ ለመሠማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በቅድሚያ በህግ ስልጣን ከተሰጠው አካል የትራንስፖርት ንግድ ፈቃድ ማግኘት አለበት፤

2/ በንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ለማከናወን ማንኛውም ሰው የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት ማሟላት የሚገባው መስፈርት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 7. የመረጃ ማዕከል ስለማቋቋም

1/ ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት የሚመለከቱ መረጃዎችን ለመሰብሰብና ለማጠናቀር የመረጃ ማዕከል ያቋቁማል፤

2/ የክልል ቢሮዎች፣ የፌዴራልና የክልል ፖሊስ አደረጃጀቶች፣ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ግለሰቦችና ድርጅቶች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከመንገድ ትራንስፖርት ጋር የተያያዘ አስፈላጊውን መረጃ በተዘረጋው የቴክኖሎጂ መሠረተ-ልማት ለሚኒስቴሩ እና ለክልሉ ማቅረብ ወይም ማስተላለፍ ግዴታ አለባቸው፤

3/ አስፈላጊውን መረጃ ለማስተላለፍ የሚረዳ የናሙና ቅፅ እና የቴክኖሎጅ መሠረተ ልማት ሚኒስቴሩ ያዘጋጃል፤ መረጃ የማስተላለፍ ግዴታ ላለባቸው አካላትም ያሰራጫል።

## 8. ስለ ሥልጣን ውክልና

1/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሚኒስቴሩ ከስልጣንና ተግባሩ በከፊል እንደ አግባቡ ለክልል የትራንስፖርት አስፈጻሚ አካላት እና ለሌሎች መንግስታዊ አካላት በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት ውክልና የተሰጣቸው አካላት በውክልና የተቀበሉትን ስልጣንና ተግባር በስራ ላይ ሲያውሉ ስለ መንገድ ትራንስፖርት የወጡ ሕጎችና ደረጃዎችን መከተልና ማክበር አለባቸው።

## 9. የተሻሩ፤ የተሰረዙና ፀንተው የሚቆዩ ሕጎች

1/ የትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

2/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ ቢኖርም በአዋጅ ቁጥር 468/1997 መሠረት ወጥተው ወይም ፀንተው የነበሩ ደንቦች እና መመሪያዎች ሁሉ ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ በዚህ አዋጅ መሠረት እንደወጡ ተቆጥረው የፀኑ ይሆናሉ።

3/ የተሽከርካሪ መለያና መመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 681/2002 አንቀጽ 15 እና አባሪው በዚህ አዋጅ ተሰርዘዋል፤

4/ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 1074/2010 አንቀጽ 7፤12 እና አባሪው በዚህ አዋጅ ተሰርዘዋል፤

5/ በተሽከርካሪ መለያና መመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 681/2002 አንቀጽ 15 እና አባሪው፤ እንዲሁም በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 1074/2010 አንቀጽ 7፤ 12 እና አባሪው ውስጥ ተደንግገው የነበሩትን ጉዳዮች በሚመለከት ሚኒስቴሩ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ዓለም ዓቀፍ ስምምነቶች መሰረት አድርጎ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናሉ፤

6/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ሌላ ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

## 10. ስለመብትና ግዴታዎች መተላለፍ

1/ የአዲስ አበባ ከተማ የትራንስፖርት ባለስልጣንና የድሬዳዋ ከተማ የትራንስፖርት ጽ/ቤት ተጠሪነታቸው ለየከተማ መስተዳድሮቻቸው ሆኖ እራሳቸውን ችለው ሥልጣን ባለው አካል ይደራጃሉ።

2/ በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/97 መሠረት ተቋቁው የነበሩት የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ የትራንስፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) መሠረት ለሚደራጁት የትራንስፖርት ተቋማት ተላልፈዋል።

## 11. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1/ በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 መሠረት የተቋቋሙና የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጣቸው የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ሰዎችና ድርጅቶች በዚህ አዋጅ እንደተቋቋሙና የብቃት ማረጋገጫው እንደተሰጣቸው ተቆጥረው ሥራቸውን ይቀጥላሉ።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ድንጋጌ ቢኖርም በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 መሠረት የተቋቋሙ ግለሰቦችና ድርጅቶች ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በዚህ አዋጅ ሥልጣን በተሰጠው አካል እንደገና መመዝገብ አለባቸው።

3/ በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/97 መሰረት ተመዝግበው የነበሩ የትራንስፖርት ማህበራት ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ ወደንግድ ማህበርነት የመለወጥና አስፈላጊውን የኦፐሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ስልጣን ካለው አካል የመውሰድ ግዴታ አለባቸው።

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3) ከተጠቀሰው ጊዜ በኋላ ማንኛውም የትራንስፖርት ማህበር ምዝገባው እንደተሰረዘ ተቆጥሮ ምንም ዓይነት ህጋዊ ሰውነት አይኖረውም።

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3) መሠረት ወደንግድ ማህበርነት የሚለወጡ የቀድሞው የትራንስፖርት ባለሥልጣኑ ዘንድ ተመዝግበው የነበሩ ማህበራት ያፈሩትን ንብረት በህግ አግባብ ወደሚለወጡበት የንግድ ማህበር ማስተላለፍ ይችላሉ።

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (5) የተደነገገው ቢኖርም በዚህ አንቀጽ መሰረት ወደንግድ ማህበርነት ሳይለወጥ የችሮታ ጊዜው ያለፈበት የትራንስፖርት ማህበር ያፈራው ንብረት ላይ አግባብነት ያለው የኢትዮጵያ የፍ/ብሄር ህግ ድንጋጌ ተፈጻሚ ይደረጋል።

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (5) ስር የተደነገገው ተፈጻሚ እስከሚሆን ድረስ በተሽከርካሪ መለያና መመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 681/2002 አንቀጽ 15 እና አባሪው፤ እንዲሁም በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 1074/2010 አንቀጽ 7፤ 12 እና አባሪው ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፤

## 12. ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

1/ ይህን አዋጅ በአግባቡ ሥራ ላይ ለማዋል የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

2/ ይህን አዋጅ እና አዋጁን መሠረት አድርገው የሚወጡ ደንቦችን በአግባቡ ሥራ ላይ ለማዋል ሚኒስቴሩ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

## 13. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም አካል ለዚህ አዋጅ እና አዋጁን መሠረት አድርገው ለሚወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች ተፈፃሚነት የመተባበር ግዴታ አለበት።

## 14. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ------------- ቀን 2014 ዓ.ም

**ሣህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ፕሬዝዳንት**